## ምድብ አራት (ከ7ኛ — 9ኛ) ክፍል
## 9 ኛ ሳምንት
## የግብፅ ስደት

**ዓላማ**

- ስለ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እና ድንግል ማርያም ስደት መማር፣

**የሚጠና ጥቅስ**

- «ልጄን ከግብፅ ጠራሁት» ሆሴዕ.11÷1

**ተጨማሪ ምንባባት**

- ሆሴ.11፣ራዕ 12 እና መጽሐፈ ስንክሳር

**መግቢያ**

- በዛሬው ትምህርት ድንግል ማርያም ከልጅዋ ከኢየሱስ ክርስቶስ እና ከዮሴፍ ጋር መሠደድዋን እንማራለን። በትምህርቱም የስደታቸውን ምክንያት፣ ያጋጠማቸውን አስቸጋሪ ሁኔታ እና ምን ያህል በግብፅ እንደቆየም እናያለን፣

**ትምህርቱ**

- ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በቤተልሔም ሲወለድ ሄሮድስ የኢየሩሳሌም ንጉስ ነበር። ኢየሱስ ክርስቶስ ንጉሥ መሆኑን ሲሰማ ሊገድለው ፈለገ። በዚህ ምክንያትም መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል ለዮሴፍ ተገልጦ እናቱ ደንግል ማርያምን እና ልጅዋን ይዞ ወደ ግብፅ እንደሸሽ በሕልም ነገረው። ዮሴፍ የታዘዘውን ፈፀመ።
- ሄሮድስ ከሁለት ዓመት በታች የሆኑ 14,000 ሕፃናትን አስፈጀ - ከእነዚህ አንዱ ክርስቶስ ነው ብሎ አስቧልና፣
- ጌታችን ከ14,000 ሕፃናት መካከል እንዳልሆነ ሄሮድስ ሲያወቀ ተከትለው እንዲይዝዋቸው ወታደሮች ላከ።
- መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል በጉዞአቸው ሁሉ ሲረዳቸው ከእነርሱ ጋር ነበር። ወንጌላዊው ዮሐንስ በግብፅ ስለነበረው ጉዞ በራዕይ መጽሐፍ እንደሚከተለው ጽፏል።
- ***«ታላቅ ምልክትም በሰማይ ታየ ፀሐይን ተጐናጽፋ ጨረቃ ከእግሮችዋ በታች ያላት በራስዋም ላይ የአሥራ ሁለት ከዋክበት አክሊል የሆነላት አንዲት ሴት ነበረች። እርስ ዋም ፀንሳ ነበር፣ ምጥም ተይዛ ልትወልድ ተጨንቃ ጮኸች። ሌላም ምልክት በሰማይ ታየ፤ እነሆም ታላቅ ቀይ ዘንዶ ሰባት ራሶችና አሥር ቀንዶችም ነበሩት....ዘንዶውም ሴቲቱ በወለደች ጊዜ ሕፃንዋን እንዲበላ ልትወልድ ባላት ሴት ፊት ቆመ። አሕዛብንም ሁሉ በብረት በትር ይገዛቸው ዘንድ ያለውን ልጅ ወንድ ልጅ ወለደች፣ ልጅዋም ወደ እግዚአብሔርና ወደ ዙፋኑ ተነጠቀ። ሴቲቱም ሺህ ከሁለት መቶ ስድሳ ቀን በዚያ እንዲመግቡአት በእግዚአብሔር ተዘጋጅቶላት ወደነበረው ስፍራ ወደ በረሀ ሸሸች።»*** ራዕ.12÷1-6
- ሐዋርያው ሴቲቱ ብሎ የገለፃት ድንግል ማርያም ስትሆን፣ ልጅዋ የተባለውም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ያሳደዳት ድራጐን ደግሞ ሄሮድስ ሲሆን በእግዚአብሔር የተዘጋጀለት ሥፍራ ግብፅ በር።1260 ቀናቱም 3 ዓመት ከግማሽ ነበር። ይህም ሄሮድስ እስኪሞት በግብፅ የቆዩበት ጊዜ ነበር።
- ድንግል ማርያም ከልጅዋ ጋር እና ከዮሴፍ ጋር ግብፅ ያረፉበት ቀን በኢትዮጵያ ኀዳር 6 ሲሆን ቁስቋም በተባለ ቦታ ነበር። መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል ሄሮድስ ከሞተ በኂላ ወደ ኢየሩሳሌም እንዲመለሱ ለዩሴፍ በሕልም ታየው። ነብዩ ሆሴዕ «ልጄን ከግብፅ ጠራሁት» ሆሴ 1÷11 ብሎ የተነበየውም ተፈጸመ።

**ማጠቃለያ**

***ክርስቲያኖች ስለ እግዚአብሔር ሊጐዱ ይችላሉ***

- ድንግል ማርያም የሰማያዊው ንጉሥ የእግዚአብሔር እናት ናት። ምክንያቱም ንጉሡ ክርስቶስን ወልዳለች፣ አብራው ወደ ግብፅ ተሠዳለች። ነገር ግን አላማረረችም ነበር። በስደቱም ምክንያት ያስተናገድዋቸው ሁሉ ተባርከዋል። እርሷ እና ልጅዋም ግብፅን ባርከዋል። ኢትዮጵያም በዚህ ጉዞ ተባርካለች። እኛም ሰዎችን በመከራቸው ወቅት ልናግዛቸውና ልንረዳቸው እንደሚገባ ያስተምረናል። እግዚአብሔር እኛንም ያግዘናል። አንድ ሰው እውነተኛ ስለሆነ ብዙ መከራን ይቀበላል። የእውነት መጨረሻዋ ግን መልካም ነው። ለዚህም ነው ጌታችን ***«እኔ ግን እላችኋለሁ፤ በሰማያት ላለ አባታችሁ ልጆች ትሆኑ ዘንድ ጠላቶቻችሁን ውደዱ የሚረግሙአችሁንም መርቁ፤ ለሚጠሉአችሁም መልካም አድርጉ፣ ስለሚያሳድዷችሁም ጸልዩ፤......»*** ያለው ማቴ 5÷44-45

***የሥልጣን ጥም አደገኛ ነው***

- ሄሮድስ መልካም ማሠብ አልቻለም ምክንያቱም ሐሳቡ በሙሉ ሥልጣኑን ማስጠበቅ ብቻ ነበር። ለዚህም ነው ሌላ ንጉሥ ተወለደ ሲባል 14,000 ሕፃናትን ያስፈጀው። ማንኛውም ምድራዊ እና ቁሳዊ ምኞቶች በአግባቡ ካልተያዙ አደገኛ ነው። በዕብሪት የሚኖሩ ሰዎች በክፉ ምኞት ስለሚያዙ በስካር እና በአደንዛዥ እፅ ይጠመዳሉ። የማይቆጣጠሩት ቁሳዊ ምኞት የሚያዳብሩ ሰዎች የሚፈልጉትን ለማግኘት ያለመታመን ባህርይን ያዳብራሉ።አንዳንድ ወንጀሎች የሚፈጸሙት ለቁስ፣ ለገንዘብ፣ ለአልኮልና ለመጠጥ.... ካለ ጠንካራ ምኞት የተነሳ ነው። አንዳንዶችም ለመታወቅ ሲሉ ብቻ ሰዎችን ይጐዳሉ።

**ጥያቄ ልምምድ፣**

1. የድንግል ማርያም የግብፅ ጉዞ የምናነበው በየትኛው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ነው::
2. ለምን ወደ ግብፅ ሸሸች
3. ድንግል ማርያምንና ልጅዋን ይዞ እንዲሸሽ ለዮሴፍ የነገረው ማነው?
4. ሌሎችን ለመጉዳትም ሆነ ላለመታመን ከሚዳርጉት ዓለማዊ ምኞቶች መካከል ምሳሌ ስጡ።
5. ምኞቶች ሁሌም መጥፎ ናቸው? አብራሩ

**ይቆየን።**